# ግንቦት ሰባት ኢሳትን ወደ መቃብር እየገፉ ነው ።

ከዘላለም ሽፈራው

የኢሳት ሬዲዮና ቴሌብዥን በሀገራችን ፓለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮች የሚጫወተው ሚና 'ቀላል አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ አሁን ያለው የሀይል አሰላለፍ በአንድ በኩል የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት ከነ ሙሉ ወታደራዊ አቅሙ የገንዘብ ሃይል ከነ ሙሉ መንግስታዊ ጉልበቱ የተሰለፈ ጉልበተኛ ሃይል እና የሕዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ በማገልገል ላይ ባለው በእሳት ራዲዩና ቴሌብዥን መሀል ያለ ትግል ነው። ይህን ሥርዓት በአለንበት ሰዓትና ጊዜ የእሳት ያህል እየታገለው፣ እያጋለጠው፣ እያደማው ያለ ማንም ሀይል የለም። ይህ ማለት የኢትዮያን ሕዝብ ፊትለፊት እያነቃ እያሰባሰበና እያታገለ ያለው እሳት ነው። በዚህ አበባሌ የፓለቲካ ድርጅቶችን ሚና ማሳነሴ አይደለም። ሆኖም አሁን ባለንበት ደረጃ እሳትና ሌሎች ሚዲያዎች፤ ለአብነትም አዲስ ድምጽ ሬዲዮ፣ ኢትዩ ሚዲያ እና ሌሎች ተመሳሳይ ሚዲያወችና ዌብሳይቶች የሚጫወቱት ሚና አሁን ካሉት የተቃዋሚ ድርጅቶች በላይ ነው ለማለት ፈልጌ ነው። እሳት በሃገር ካለው አድማጭ ሕዝቡ ለእሳት ከሚሰጠው መረጃ በውጭ ኢትዮጵያዊ ከሚሰጠው ድጋፍ እንጻር እሳት ሬዲዮና ቴሌብዥን የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል። አለመታደል ሁኖ ፓለቲካዊው ሚድያውን መምራት ሲገባው ሚዲያው የፓለቲካ ድርጅቶችን እየመራ ነው ።ይህን ካሉክ ወደ ተነሣሁበት ጉዳይ ልነሳ።

እሳት ራዲዮና ቴሌቪዥን ለምን አላማ፣ በነማን ጥረተ እንደተቆቋመ እና ዛሪ በማን እጅ እንደወደቀ ቢታወቅም። ራዲዮና ቴሌቪዥን በባለሙያወች የሚከናወን በመሆኑ እሳት በሚሰራው ሥራና ኣስተዋጽዖ እንጅ ማንም የእሳትን የባለቤትነትና ተቋሙን ከኋላ ሁኖ የሚመራውና የሚስተዳደርው ማነው ብሎ የጠየቀ አልነበረም። ዛሬ ግን ያገጽታው መቀየሩ ለማንም ስውር ስላልሆነ ልንጠይቅ ተገደናል ። እሳት ሬዲዮና ቴሌብዥን ሕዝብ ከሰጠው ከበሬታ፣ እምነት የሀገራችን ሁሉን አቀፍ ችግር ያለ አድልዎና በገለልተኝነት ያደርግ የነበረው የመረጃና የዜና አቀራረብ በተቃዋሚ ድርጅቶችና በሕዝቡ ብቻ ሳይሆን የገዥው ክፍል ማለት ወያኔ ኢህአዴግ ሳይቀር እንደአንድ ከፍተኛ ተቋም በመቁጠር ለዚህ ሚዲያው ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ይሰጡ ነበር። በዚህ ተጠቃሚው እንደ ሚድያ እሳት እንደ ትግል የተቃውሞ ጎራ ተጠቃሚዎች ነበሩ። ምክናያቱም ወያኔ/ኢህአዴግ የቆመበት እውነትኛ መሠረት ስሌለው በሚዲያ በቀረበ ቁጥር ይበልጥ ራሱን ያጋልጣል። እንዲህ አይነት ሚዛኑን የጠበቀ የመረጃና የዜና ትንታኔ ያቀርብ የነበረው እሳት በጣም ተናፋቂና ለቀጣይነቱም ሕዝቡ አይናችንና ጆሮችን ነው በሚል መርህ ሙሉ ድጋፍ ቸሮታል። የሕዝብ ከበሬታ እና እምነት ዛሬ ተቀይሮ ሚዲያው በአሁኑ ሰዐት በአሳሳቢ መንገድ እየተጓዘ ነው በሚል ተተክቷል። ለዚህ የአስተሳሰብ ለውጥ አይነተኛ መነሾ ከሕዝብ ልሣንነቱ ወደ ድርጅታዊ ልሳንነት በመቀየሩ ሲሆን፤ የነበረውን የሚድያ ደረጃውን በፍጥነት በማሽቆልቆልና በመውረድ ተሰሚነት፣ ተአማኒነቱን እያጣ ነው የብዙ ዜጎች ግምት ሆኗል።

ቀደም ብየ እንደገለጽኩት የእሳት ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሚተዳደረውና የሚመራው በግንቦት ሰባት የፓለቲካ ድርጅት መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ይህ ሁኖ ግንቦት ሰባት ሙሉ የፓለቲካ ተፅእኖ በእሳት ላይ ሳያሳርፍ እሳት በጨረፍታ በሚደረግለት የሚዲያ ሽፋን ተጠቃሚ ነበር ። በሙያው የተካኑ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ በሚፈልጉ ወጣት ጋዜጠኞች ለተአማኒነትና እድገቱ እንዳልደከሙበት ሚዲያው ሰለባ በመሆን ከሕዝብ ልሳንነት ወደ ድርጅት ልሳንነት እና ብሎም የፕሮፓጋንዳ ማሣሪያ ሲሆን፣ ጋዜጠኞችም ሙያው ከሚፈቅድላቸውና ህዝብ ከቸራቸው አመኔታ በመውረድ የግንቦት ሰባት ተኪ ካድሬወች ሲሆኑ፤ የሚዲያውም ለዛና ውበት፤ ሕዝባዊነቱንና የነፃነት አብሳሪነቱን በሚያሳዝን ንደውታል። ለዚህ ታላቅ አስተዋጸኦ አበርካች ሚዲያ አሁን ካለበት ሁኔታ የከተተው አቅጣጫውና ውሉን አጥቶ በዳበሳ የሚተራመሰውን የግንቦት ሰባትን ድርጅት ነብስና እስትፋንሽ እሰጣለሁ በሚል ሚዲያው እራሱም ወደ አደገኛ ጉዞና ውድቀት እያመራ ለመሆኑ ብዙ ሁነኛ ዜጎች በማሳሰብ ላይ ለመሆናቸው የኢትዮጵያውያን ቁብ ሳይቶችን ማየት በቂ ይመስለኛል። ግንቦት ሰባት እውነትኛ ትግል አድርጎ የኢትያጵያን ሕዝብ አደራጅቶ ታግሎ በማታገል ለነጻነታችን የሚደርስ፤ መርህ ኖሮት መሬት ላይ እየሰራ ያለ ድርጅት ቢሆን ንሮ ሁላችንም እንደ ዜጋ ከጐኑ በተሰለፍን ነበረ። ነገር ግን ይህ ድርጅት ሀገራዊ ሃላፊነት በማይሰማቸው ለሀገራችን ሉዓላዊነትና የሕዝብ ጥቅም ግድ በሌላቸው ግለሰቦች ስር ሲሆን። እንደድርጅትም ቢሆን ረጅምና ውስብስቡን ትግል አስልቶ እየሰራ ያለ ድርጅት ሳይሆን በሆታና በጫጫታ በዕለት የፕሮፖጋዳ ፍጆታ ውሎ የሚድር ድርጅት በመሆኑ ነው። እስከ አሁን በተጓዝነው ግንቦት ሰባት የኢትዩጵያ ሕዝብ በሚካሄደው የነፃነትና የዲሞክራሲ ትግል ለፈፀመው በደልና ማጭበርበር ውሉን የሳተው እሳት ሙሉ ተባባሪ በመሆኑ የድርጅቱን ችግሮች እና አስጠያቂ ኩነቶችን ሁሉ አስወግዶ ካልሰራ ሕዝብ ፈቃደኝነቱን የሚነፍግ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። እሳት የግንቦት ሶባትን ገድል በየጊዘው ያደረጋቸውን ወታደራዊና ፓለቲካ ውጤቶች

እየዘገበልን ቢሆን ደስተኞች ነበርን። ያንን ኩነት ግን እያየን እንዳልሆነ ጭብጥ ሁኔታው መስካሪ ነው። ድርጅቱ (ግንቦት 7) ከጅምሩ ምንም ሳይኖረውና አንድ ጋት መሬት ለነጻነት ሳያሳየን በትዕቢትና በእብጠት መወጣጠሩ፤ኢትዩጵያውያን ድርጅቶችን መናቅና በማንኳሰስ፤ በተግባር ትብብር ሲጠየቅ መሬት ላይ ከሚሰራ ድርጅቶች ጋር ነዉ የምሠራ በማለት ከኢትዮጵያ ነጻ መውጣት እንፈልጋለን ከሚሉት ከነ ኦነግ፤ የኦጋዴን ነፃ አውጭ፣ እና ከሱማሌ ነፃ አውጪ ጋር በመተባበር። በየ ስብሰባው መድረክ የነዚህን የተገንጣዮች ባንዲራና ዓርማ እንድንሸከም አድርጎናል። ከእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ እንዲሉ፤ የየስብሰባወች ተጋባዥም ሆነ የገንዘብ ድጎማውን የሚያወጣው የነዚህ ተገንጣይ ድርጅቶች አባላት ሳይሆኑ ለአገሪቱ አንድነትና ለሕዝብ ነጻነት ምኞት ያለው አንድ ሀገር፣ አንድ ሕዝብ የሚለው ክፍል ነው። የአገር ጠላቶችን ባንዲራም እንዲሸከም። የመሪወቻቸውን መጓጓዣ፤ የስብሰባ አዳራሽና ማነኛውንም ወጭ እንዲሸፍን የሆነውም ይህ ለአገሩ ቀናኢ የሆነ በውጭ የሚኖር ዜጋ ነው።

የግንቦት 7 አሳዛኝ ተግባራት ሁሉ በመጀመሪያ እረድፍ የሚታየው የእሳት ሬድዮና ቴሌብዥን ኢትዮጵያ አንድነትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶችን ዕድልና እውቅናን በመንፈግ ከግንቦት ሰባት ጋር በማበርና በመቀናጀት የሆታና የጫጫታ ፕርፓጋንዳ ሆያሆየው ደርቶ የከረመው ተገንጣይና ኢትዮጵያን የሚጠሉ ድርጅቶች ጋር የግንቦት ሰባት መሪወች ያደረጉት መዳራት እንደፖለቲካ ትብብር በመዘገብ ነበር (ኦነግንና የኦጋዴ ነጻነት ግንባርን ያስታውሷል)።

እንደሚታወቀው ግንቦት ሰባት ከነፃነት አውጭ ድርጅቶች ጋር ያደረገው ሕብረትና መተሳሰር በእሳት ብዙ የተዘመረለትና የተነገረለት ሲሆን። ኢትዩጵያዊያን ድርጅቶችን አንገት እንዴደፉ፣ ኢትዮጵውያን ዜጎች በማንነታቸውና በሀገራቸው አንድነት ብዥታ በመፍጠር ነፃ አውጪዎችን እንድንቀበልና እንድናምን የተደረገ ሥነ ልቦናዊ ጦርነት ነበር። በሌላ በኩል ለአገሪቱ አንድነትም ሆነ ለሕዝቧ ነጻነት ብዙ ፋይዳ የማይሰጠው ግንቦት ሰባት ይህን የሚደርገው ወዶ ሳይሆን የሚቆምበት መሬት፤ የሚይዘውና የሚጨብጠው ስሌለው። ጠበቅ ብለን ስንመረምር የድርጅቱ መሪወች በመርህ የሚመሩ ባለመሆናቸው ባዶነት የሚሰማቸው እና በሆይ ሆይታ ሕዝብ ፊት ያቀርበናል ያሉትን ሁሉ፤ ከሰይጣንም ጋር ቢሆን ሊጎዳኙ እንደሚችሉ እኔ ሳልሆን ደጋግመው በየስብሰባው መድረክ የተውገረገሩበት ቃል ነው። ለዚህ ነው ሰሞኑን እስከስታቸውን ወደኋይላ ቀይረው የእሳት ጋዜጠኞችን ወደ ምድረ ኤርትራ በመውሰድ ድርጅቱ ከአርበኞች ጋር ግንባር ፈጠረ በሚል አርበኞች ግንቦት ሰባት ተመሠረተ የሚል ፕሮፖጋዳ ሲሰራጭ የከረመው።

ለአስራ አምስት ዓመታት በኤርትራ በርሃ አለ እየተባለ የሚነገርለት አርበኞች ግንባር ከሚጠበቅበት ውጤት አንድ ኢንች ያልተንቀሳቀሰ ቢሆንም፤ ለሮፖጋንዳ ፍጆታ እና አሉ ለመባል አልፎ አልፎ ከወያኔ ወታደሮች ጋር ተጋጨ የሚል ዜና ሲያቀርብ ቆይቷል። ይህችን የተማረው የግንቦት ሰባት ፓፐላር ፎርስ በኢንተርኔት የትንሽ ሰዎች ምስል በኢንተርኔት ደጋፊ ሚዲያወች ሲያሳየን ቆይቷል። ሌላው አስቂኝ ድራማወች የድርጅቱ ሊቀመንበርና የአሁኑ የግንባሩ ኮማንደር ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ከሚሰጡት ዛቻና ተስፋ ውጭ ሠራዊታቸውን ሲጎበኙ ወይንም ሲያበረታቱ የሚያሳይ ምንም ምስል እስካሁን አላየነም። ትዝ ይላችኋል ካሊፎርኒያ በአመታዊ የእሶርት በአል የዋናው ጸሀፊ በጠላት እጅ መውደቅን ምክንያት በማድረግ ያደረጉት ፉከራ? በበኩሌ ያን እለት ጫካ ገብተው የሚያድሩ። የወያኔ ጄሌወችን በየ አሉበት ዋጋ የሚያስከፍሉ መስሎኝ በወኔ ተከትያቸው ነበር።

አንድ ትልቅ ነገር የተገነዘብሁት ቢኖር ከወያኔ የማይተናነሰው ያገራችን ሁነኛ ጠላት የኤርትራ መንግሥት በምን ስሌትና ቀመር እንደሆን ባይገባኝም ከወያኔ ጋር ጦርነት ብገባ ግንቦት ሰባት ድርጅትና እሳት ሬዲዮና ቴሌብዥን ይጠቅሙኛል የሚል እምነት አለው። እንደሚመስለኝ (መቸም መላምት አይከለከልምና) ሻቢያ የባድመ ጦርነት ኪሳራ ያደረገኝ የተሳሳተ ስሌት ተጠቅሜ ነው። ይህውም የኢትያጵያ ሕዝብ የህዋት ኢህአዴግን መንግሥት እንደ ማይፈልግና እንደ ሚጠላ በማሰብ በጦርነቱ ተባባሪና ተሳታፊ አይሆንም በሚል ስሌት ነበር ወደ ጦርነት የገባሁት። በጦርነቱ ያየሁት ግን የኢትዩጵያ ሕዝብ በኤርትራ መንግሥትና ሻቢያ ላይ አቂሞ ሀገራችንን ለመከፋፈል ወያኔን አዲስ አበባ ሚኒሊክ ቤተመንግስት ያስገባው፣ እኛንም ለውርደት የዳረገን ሻቢያ ነው በሚል ወግቶናል። ለውደቀትና ለኪሳራም ዳርገውናል። ስለዚህ አሁንም ቢሆን ወደ ማይቀረው የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ይህን ክፍተት በመሙላት ያለፈው በኤርትራ የተፈጠረው ኪሳራ እንዳይደገም ማድረግ የምንችለው የግንቦት ሰባት ድርጅት እና የእሳት ራዲዮና ቴሌብዥንን በመጠቀም ነው ብለው ያምናሉ ። ሻቢያ ከሌላው የተቃሚ ድርጅቶች ግንቦት ሰባትን የመረጠበት ምክንያትም ድርጅቱን መሪዎች በኡትዮጵያ ሕዝብ ይታወቃሉ ይደመጣሉ በሚል ስሌት ሳይሆን፤የሆያሆየና የአየር ባየር ታጋይነታቸውን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ። ብሎም ለአገር ሉ አላዊነት፤ ለሕብ ነጻነትና ለመርህ ደንታ እንደሌላቸው የኦጋዴን ነጻነት ግንባርንና የኦሮሞ ነጻአውጭ ሐይላትን አዝለው ሲዞሩ በመታዘቡ ነው። እናም የድርጅቱ መሪወች መሪ መሆናቸው ከታሰበላቸው ብሎም ትንሽ ጉርሻ ከተሰጣቸው ማንኛውም ሥራና ተግባር እንደሚፈጽሙለት በማመን ነበር። ኢሳያስ

አልተሰሳተም በእርግጥም እነ ዶክተር ብርሃኑ የእሳት ጋዜጤኞችን ኤርትራ ድረስ በመላክ የእነርሱን ቆሻሻና ልቅላቂ በእሳት ትክሻ እንዲወድቅ አደረጉለት። ኢሳያስ በበኩሉ ጆሮ አይሰማ የለምና ድርጅቱ ትንሽም እስትንፋስ ያገኝ ዘንድ አርበኞች ግንባርን እጅ በመጠመዘዝ ከግንቦት ሰባት ጋር ተዋሀደ ተባለ (ሙት ለሙት አብረህ አዝግም ይሉታል የኢሳያስ ጨዋታ ይህች ነበረች)። የዚህ ታሪካዊ ድራማ ውጤት ግንቦት ሰባት ሠራዊት ኣለው ለመባል ነበር ያም በጌታ ኢሳያስ ተከወነ ማለት ነው። ግን ግን ለአስራ አምስት አመት አንድኢንች መሬት ያልያዘው የአርበኞች ግንባር ጭራሹን የግንባሩ መሪና ኮማንደር የኒውዮር/ኒውጀርሲ ነዋሪው ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ሆኑ አሉን (እዚህች ላይ ኢሳያስ ትልቅ ግፍ ነው የሰራ ግን መቸስ ዶክተሩ ገና አልገባቸውም ማለት ነው)። አፍ ያለው ያግባሽ ወይከብት ያለው የሚለውን ተረት ያስታውሰናል። ከዚያማ በኋላ ያየነው እሳት ኤርትራ መሬት ሆኖ ያስተላለፈው ፕሮግራም እዚህ በዩናይትድ ስቴትስ በመዘዋወር የምናየው አቢይ መልዕክት የሚያተኩረው ፕረዘርዳንት ኢሳያስ ለኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና ሉዐላዊነት እንደሚጨነቁ። ወያኔ አግልሏቸው እንጅ አሁን ያለው በዘር ላይ የተመሠረተውን መንግሥትም ሆነ ስአት እንደማይፈልጉት፤ ስለታታሪ ሰራተኝነታናቸው እሩህረነታቸው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የዲሞክራሲ ስርአትና ሰላም አለመኖሩ እንደሚሳስባቸው፤ ይህን ለመለወጥ ከሌሎቹ ተቃዋሚወች ጋር እየሰሩ ስለመሆኑ ማየት ማመን ነው በሚል ፈሊጥ
ልጅ መሣይ መኮነንና፣ ፋሲል የኔዓለም እንደ ባለሙያው ጋዜጠኛ ሳይሆን የሰጡት ምስክርነት፤ ማሲንቆውን ይዞ ሽልማቱን እንደ ሚጠብቅ የስፈር አዝማሪ ለዘመናት በትግል ላይ ያሉትን ድርጅቶች እንኳን የሉም ብንል። በኤርትራ በረሀወች የወደቁት የሰራዊት አባላት ጓደኞችና ቤተዘመድን ምን መልስ እንደምንሰጥ በማይታወቅ መልኩ፤ አንድ ጋዜጠኛ ሊከውን ከሚገባው ተግባር ይልቅ እንደ ተራ አዝማሪ ሲቀላምዱ መታዘባችን በእውነት እንደአንድ ዜጋ እኔን አሳዝኖኛል። እንደዛ የምናከብራቸው ናዝግጅታቸውን በናፍቆት በጉጉት የምንጠብቅላቸው ጋዜጠኞች ድምፃቸውን ለመስማት እስክንጠላቸው ድረስ ግንቦት ሰባት መቀለጃ ሲያደርጋቸው ማየትም ሌላው አሳዛኝ ተውኔት ይመስለኛል።

ለእሳት መፈጠርና መቀጠል ግንቦት ሰባት የተወሰነ አስተዋፆኦ አድርጎ ይሆናል። እሳት የቆመው ግን በሃገር ወዳድ ኢትዮያዊ ድጋፍና እርዳታ ነው። በአነግ ወይም ነፃ አውጭ ነን በሚሉ በተባባሪ ድርጅቶች አይደለም ።ስለዚህ እሳት የሕዝብ ንብረትና ልሳን በመሆን ለዲሞክራሲ ናለነፃነት ለሚደረገው ትግል ትክክልኛ መረጃና ኢንፎርሚሽን በማቅረብ በትግሉ ሥራውንንና አሻራውን ማስፈር አለበት። የግንቦት ሰባት ድርጅትም የሕዝብን ሀብት የሆነን ሚድያ እየጐተተ እርሱ ከገባበት አሮንቃ ማስገባት የለበትም። በግንቦት ሰባት የተሰባሰባችሁ ሀገር ውዳድ ኢትዮጵያውን ድርጅታችሁን ወደ ውስጥ ልታዩትና ልትገመግሙት ይገባል። የድርጅቱ አባል የውስጥ አቅሙንና እንቅስቃሴውን አውቆ ካልታገለ ዋጋ የለውም ።አባሉ ለሕዝብ በሚተላለፍ
የድርጅቱ ፕሮፖጋዳ ራሱን አሳምኖና መረቅኖ የሚኖር ከሆነ እየታገለ ሳይሆን እየተደበረ ነው። ጠላታችን ወያኔነን ማሸነፍ የሚቻለው ከእርሱ በላይ ጠንክሮ ሲሰራ እና ታግሎ የሚታግል መሪ እና አመራር ካልተፈጠረ የትም አይደስም። ራሱን ከወያኔ ሰርጎ ገብና ከደህንነት ጥቃት የማይከላከል ድርጅት የትም አይደርስም። ግንቦት ሰባት ከራሱ እስከ አንገቱ በወያኔ ደህንነት የተዘፈቀና የተበከለ ስለመሆኑ በድርጅቱና በዜጐቹ ያስከተለውን ሰለባ በቅርብ እዘግበዋለሁ። በዚህ ዘገባየ አንዳንድ ወገኖች ወያኔን ማሳወቅና ማስደሰት ነው ሊሉ ይችላሉ። እውነቱ ግን ወያኔ ስለ ግንቦት ሰባት ድርጅት ውሎና አዳሮ ሳይሆን የሚያውቀው። ከተራ አባላት እስከ እነምናምኑ አለበት ማለት ድፍረት አይደለም። ይልቁንም ዘገባው ስለዚህ ድርጅት አካሂድ አቅምና እውነታ ህሊናችንና ልቦናችን እያወቀ ለማረም፣ ለመገምገም፣ ለመተቸት፣ ድፍረትና ወኔ ላጣን ዜጎችና ለድርጅቱ አባላት የተወሰነ ግንዛቤ ለመስጠት ነው። መነሻዬ ግንቦት ሰባት በባዶ ሜዳ ራሱን አሳብጦና ቆልሎ በአየር ባየር ፖለቲካና ፕሮፖጋዳ ሕዝብና ደጋፊውን ሲዋሽ ከርሞ አሁን ነገሮች እያፈጠጡ ሲመጡ የሕዝብ ንብረት የሆነን እሳትን ከዚህ ቀውስ ማስገባት ወንጀል ሆኖ ስለተሰማኝ የእራሴን አስተያየትና ምክር ለመለገስ ሲሆን። የእሳት ራዲዮና ቴሌብዥንም ሕዝብ የሚዳምጣችሁ የሚፍቅራችሁና የሚረዳችሁ በተለይ ከግንቦት ሰባት ጋር ባላችሁ ግንኙነት ሳይሆን ኣማራጭ ሜድያ በመሆናችሁና የኢትጵያ ሕዝብ ልሳና ጆሮ ናችሁ በሚል ነው። አለዚያ ይህ ሕዝብ ማውጣትና ማውረድ በጣም ያውቅበታል። መሆንና መምሰል በጣም ይለያያል። እሳቶች መሆንን እንጅ መምሰልን አልቻላችሁበትም። ሕዝብ ሁሉን ያውቃል የሕዝብን ግንዛቤና ዕውቀት የሚንቅ ወይንም የማያገናዝብ ሚድያ ራሱን እያጠፋ ይሄዳል። እሳት ራዲዮና ቴሌቪዥን እንደ ኢቲቪ እንዲናቅ የሚፈልግ ጤነኛ ዜጋ ኣይኖርም። በመጨረሻም ፅሁፌን የምደመድመው እኔም እንደ መሣይ መኮንን ኢትዩጵያ ለዘላለም ትኑር በሚል ነው። ግን እኔ ከምሬ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘለአለም ትኑር!!!